ነሐሴ 25 1998 ዓም

ከኮ/ አሰናቀ እንግዳ የዘጠና ሦስት ዓመቱ ሽማግሌ ማሳሰቢያ

ይድረስ:- በውጭ ሀገር ላላችሁ የወያኔን ቡድን እነ መለስ ዜናዊን ለምትደግፉ የትግራይ ተወላጆች ወንድሞቸና እህቶቸ::

## ልመስክርላችሁ ወይስ ልመስክርባችሁ?

እኔ የትግራይን ክፍለ ሀገርና የኤርትራን አውራጃዎች ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ የመሬት አቀማመጥና የሕዝቡን ባኅል ÷ ወግና ልማዱን በመዘዋወር ያየሁና የተረዳሁ የዓይን ምስክር ነኝ::

በትግራይና በኤርትራ በደጋው ሕዝብ መካከል÷ የዘር÷ የባኅል የቋንቋ÷ የስም አወጣጥ÷ የመልክና የጠባይ የወግና ልማድ የምጣኔ ሃብት ይዞታም የማኅበረሰብ ተቋማትም አንድ ናቸው:: ልዩነት የላቸውም :: በኤርትራ ቆላም የሚኖሩት ትንንሽ ብሄረሰቦችም ቢሆኑ በብዙ ነገሮች በደጋው ከሚኖረው ሕዝብ ጋር ይመሳሰላሉ:: ብሔረሰቡንም አንድ አድርጎት የኖረው÷ ተፈጥሮ ነው:: መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብም አብሮ እንዲኖር ያደረጉት በርካታ የአንድነት ክሮች ነበሩት:: ያም በመሆኑ ዛሬ የመለስ ቡድን በኅሳ ሊከፋፍለው የሚያደርገውን መሰሪነት በመቃወም በዘረኝነት ወጥመዱ ሊገባለት አልቻለም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት መለስንና ግብር-አበሮቹን በመቃወም ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ አይከፍሉ መስዋዕት እየከፈለ በመታገል ላይ ይገኛል:: መላው የትግራይ ጀግና ሕዝብም የዚህ ሀገራዊ ትግል አካልና አምሳል እንደሚሆን አልጠራጠርም:: ምክንያቱም ቀደም ሲል በተመዘገበው የሀገራችን የነፃነት ትግል ታሪክ ተገቢውን ምዕራፍ በደሙ የፃፈ የትግራይ አርበኛም ጭምር በመሆኑ ነው:: ይህን ታሪካዊ ሀቅ የመለስና ቡድኖቹ የዘረኛ ሥርዓት ሊፍቀው ቀርቶ÷ ሊያወይበው ከቶ አይችልም:: አስተዋዩ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም የመለስን ከፋፋይና አጥፊ ተግባር÷ከሰፊው የትግራይ ሕዝብ ለይቶ ማየትና መፍረድ የሚችለውም በዚህ መሠረታዊ ምክንያት ነው:: የወያኔ መሪዎች እነ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለሚፈጽሙት ብሔራዊ ወንጀል ተጠያቂዎቹ እነርሱ እንጅ ÷ የትግራይ ሕዝብ አይደለም:: ይህንን ሀቅ የሚስቱ ካሉ አመለካከታቸውን ሊያስተካክሉ ይገባል እላለሁ::

የወያኔ አመራር ቡድኖች ካንድ ኅጥ የወጡ የመንደር ልጆች ናቸው:: በዚህም ምክንያት ነው የመገንጠልን ዓላማ ተግባራዊ እያደረጉ÷ የሀገሪቱን ዜጎች በኅሳ እየከፋፈሉ÷ ብሔራዊ ሀብቷንም እየዘረፉና እያሸሹ ተራ ወንጀለኞች የሆኑት:: ጠባብነታቸው ከኅጥ ባሻገር ማየት ስለአላስቻላቸው÷ በዙሪያቸው ያካባቢ ኅጠኛ መንግሥታት እያቋቋሙ የኢትዮጵያን መጥፋት ዘለዓለማዊ ለማድረግ በመጣር ላይ ናቸው:: እነርሱ የጠፏታል እንጅ ኢትዮጵያ ሀገራችን ግን አትጠፋም:: ልጆቿም አይበታተኑም:: የትግራይ ሕዝብም÷ ኢትዮጵያን በነ መለስ ዜናዊ እጅ እንዳትጠፋ የሚጠበቅበትን የሀገር አድን ተልዕኮውን ይፈጽማል እንጅ÷ ከዚህ የተለይ ሌላ ጥቅም የለውም:: ዛሬ ለነመለስ ዜናዊ ብሔራዊ ወንጀል አባሪና ተባባሪ በመሆን በካድሬነትም ሆነ በነፍሰ-ገዳይነት የሚያገለግሉ ጥቂት የትግራይ ክፍለ ሀገር ተወላጆች ብቻ ሳይሆኑ÷ ከሌሎች ክፍላተ-ሀገር የተወለዱም ጭምር መሆናቸው የሚካድ አልሆነም:: የጥቅም ተካፋይ የሆኑም ያልሆኑም በትግሬነታቸው ብቻ ለመለስና ቡድኖቹ ያልተቆጠበ ድጋፍና ትብብር የሚያደረጉ የትግራይ ሰዎች ቁጥራቸው የሚናቅ አይደለም:: በቀውጢ ሰዓት÷ ደጋፊ ይቅርና መሬት እራሷም ስለመትከዳ÷ ከወያኔ ጋር ተያይዘው እንዳይጠፉ÷ ከአሁኑ እንዲያስቡበት ከፀፀት ነፃ የሚያደርገኝን አባታዊ ምክሬን

አስተላልፋለሁ። የአፄ ኃይለ ሥላሴንና የደርግን ፍፃሜ መንግሥታት ለተገነዘበ ብልኅ ዜጋ፥ ብዙ ትምህርት ሊገነዘብ ይችላል። የወያኔ ሥርዓት ፍፃሜም የተለየ ሊሆን አይችልም። በየትኛው የታሪክ ሂደት ውስጥ በማነኛውም ኅብረተሰብ ታሪክ፥ በየአንዳንዱ አስራ ሁለት ሃዋርያት መቸም  አንድ አንድ ይሁዳ ጠፍቶ አያውቀም።  ኢትዮጵያ ሀገራችንም፥ የዓለም ኅብረተስብ አባል እንደ መሆኗ፥  ከዚህ ክስተት ነፃ ልትሆን አትችልም። ሀገራችን በረዥም ዘመን ህልውናዋ፥ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች፥ ሀገራችውን በክፉ ቀን እያጋፈጡ ፥ እየካዱና እያጋለጡ ለባዕድ ወራሪ በመሸጥ አሳፋሪ ተግባር የፈፀሙ ዜጎች ነበሯት። ስማቸውን ከነማስረጃ መጥቀስ ግን በአሁኑ ወቅት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም።  ታሪክ መዝግቦ ስለአቆየው፥ ከታሪክ ማኅደር ማግኘት የሚቻል ይመስለኛል።

መገንዘብ የሚገባን ቁም ነገር ግን ዛሬም እንደ ትላንቱ፥  ሕዝባቸውን ከሚበድልና ሀገራቸውን ከሚጎዳ ሥርዓት ጋር አባሪና ተባባሪ ሆነው የሚያገለግሉ ግለሰቦች መኖራቸው ነው። የወያኔ አጥፊ ሥርዓት የወንጀል ግብረ-አበር የሆኑት ዜጎች ደግሞ፥ ከትግራይ ብቻ ሳይሆኑ ከየትኛውም ኅብረተስብ የተውጣጡ የጥቅም ተገዥዎች ናቸው። ለአላፊ ጠፊ ጊዜያዊ ጥቅም  ሲሉ ኅሊናቸውን ብቻ ሳይሆን፥ ሰብዕናቸውንና ታሪካቸውን እየሸጡ ሕዝባቸውን እየጎዱ ያሉ የመለስ ዜናዊ ወያኔ ሥርዓት አገልጋዮች፥ ወደዱትም ጠሉት፥ ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ እያሳዘኑ፥ ኢትዮጵያ ሀገራቸውንም እየጠፉ መሆናቸውን ሊያውቁት ይገባል። ይህንንም ወንጀላቸውን በግልፅ የሚነግራቸውና ከአጥፊው ሥርዓት ጋር በታሪክ እንዳይፈረድባቸው አበክሮ የሚመክራቸው የሀገር ሽማግሌ ያስፈልጋል። ይህንን ግልፅ ደብዳቤ ለማፃፍ ያነሳሳኝም የሽምግልና ኃላፊነቴን ከመወጣት አኳያ እንጅ፤ ሌላ ምንም ምክንያት ኖሮኝ አይደለም። በዚህ አረጋዊ ዕድሜ የፖሊቲካ ሥልጣንም ይሁን የሀብት ጉጉት የለኝም። ኖሮኝም አያውቅም። ከሕሌና፥ ከታሪክና ከትውልድ ወቀሳ ነፃ የሚያደርገውን ሁሉ አድርጎ ከዚህች ውጣ ውረድ ከበዛባት ምድራዊ ዓለም በሰላም መለየት ግን የማነኛወም ሰብዓዊ ፍጡር መሠረታዊ ዕምነትና ተልዕኮ ሊሆን ይገባል የሚል ፅኑ ዕምነት አለኝ።

ኢትዮጵያ ሀገራችን  በረዥም ዘመን ታሪኳ፥ በተለያየ አጋጣሚ የባዕድ ወራሪዎችን የተቋቋመችው ጀግኖች ልጆቿ ተባብረው በመቆማቸው እንጅ ሌላ ብልሃት አልነበረውም። ዛሬም ያ ሀገራዊ ዓብነት በበለጠ ጠንክሮ መቀጠል ይኖርበታል እንጅ፤ ዜጎቿ በጎሳ ተከፋፍለው፡ ለጠላቶቿ ምቹ የሚሆነውን ተግባር መፈፀም የለባቸውም።  ሀገራችን በታሪኳም ቢሆን በተለያዩ አምባገነን ገዥዎች ሥር አልፋለች።  ነገሥታቱ ሁሉም ለሥልጣናቸውና ለዘውዳቸው ቀናዒ እንደነበሩ የሚካድ ባይሆኑም፤ ህዝብን በማስተዳደር በኩል ግን፥ሁሉም ተመሳሳይ የሆነ ተግባር ይፈጽሙ ነበር ለማለት አይቻለም። እንደ የባኅሪያቸው አንዱ ርኅሩኅ ሌላው ጨካኝ፥ አንዱ ፈርኃ እግዚአብሔር የነበረው ሌላው ፀላዒ-ሰናይት የተላበሰ ነበር። ሁሉንም አንድ የሚያደረጋቸው  ግን የጋራ ባኅርይና ተግባር፥ ዓላማና ግብ ነበራቸው። ይህ በጋራ የሚካፈሉት ማንነት ደግሞ ኢትዮጵያን አንደ ሀገር፥ ሕዝቧን እንደ ሕዝብ በጋራ ሀገራቸው እንዲኖሩ ረድቷል። ዳር ደንበሯንም በተቻለ መጠን ሳይደፈር እንዲቆይ አድርጓል።  ማነኛቸውም ነገሥታት፥ ሀገራቸውን እንደ ወያኔ  ሆን ብለው ለባዕድ አልሸጡም። ሀገርም አላስገነጠሉም። ከአቅም ማነስ የተነሳ ካለሆነ በቀር፥ የሀገራቸውንም ድንበር አላሳደፈሩም። እንደነ መለስ ዜናዊ  በዕቅድ ሀገራቸውን አላስገነጠሉም። ሁለት ወንድማማቾቹን አላላያዩም። ሕዝብን በጎሳና በሃይማኖት፥ በቋንቋና በጎጥ አለከፋፈሉም። የሀገራቸውንም አንድነት አላናጉም። የኢትዮጵያን ጠረፍ አላስደፈሩም።  ለዚህም እንደ ታላቅ የታሪክ ዓብነት የሚጠቀሰው፥   መጋቢት ሦስት ቀን 1881 ዓም  የማህዲዎችን ወረራ ለመመከት በተደረገው የመተማ  ጦርነት ማስዋዕት ሆነው የሀገራቸውን ጠረፍ ያስከበሩትን የሰማዕቱን የአፄ ዮሐንስ አራተኛን ታሪክ መጥቀስ ብቻ ይበቃናል። የታሪክ እንቆቅልሽ ሆነና ትላንት ዮሐንስ አራተኛን የፀነሰች የትግራይ ማህፀን ዛሬ በዘመናችን ከሀዲዎቹን እነ መለስ ዜናዊን ማብቀሏ  ግን በእጅጉ ያሳዝነኛል።

በመጨረሻ  ላሳስብ የምፈልገው የታሪክ ግንዛቢዎች ይኖሩኛል። ይኸውም፥

- መረጃ በማቀበል ከሆነ፥ ያዳዋን ድል በማስገኘት ከፍተኛ ሚና እንደ ተጫወተው እንደ አዋሎም መሆን፥

- የአትዮጵያን ጠረፍ በማስከበር ከሆነ ፥ "ማህሉ ገነት ዳሩ እሳት" ብለው ጣሊያኖችን ድል እንደመቱት እንደ አሉላ አባ ነጋ መሆን፥

- ቆራጥነትን በማሳየት ከሆነ፥ እንደ ሞገስ አስገዶምና አብረሃ ደቦጭ በግራሲያኒ ላይ ቦምብ በመወርወር መስዋዕት መሆን፥

- የኢትዮጵያን ክብርና ታሪክ በማስከበር ከሆነ፥ እንደ ዘረዓይ ድረስ በሮማ ከተማ የጠላትን አንገት በጎራዴ በመክላት የጀግኖች ጀግና መሆን፥

- በዲፕሎማሲው መስክ አኩሪ ታሪክ በማስመዝገብ ከሆነ፥ እንደ ብላቴን ጌታ ኤፍሬም ተወልደ መድኅንና እንደ መብርሃቱ ሎሬንሶ ታዕዛዝ የሀገራቸውን ጉዳይ በዓለም ሸንጎ አቅርቦ በመሟገት አኩሪ ታሪክ በማስመዝገብ የተራቀቀ ዲፕሎማት መሆን ይገባል እላለሁ። ከዚህ በቀር፥
- የመለስ ዜናዊ አገልጋይ በመሆን ሀገርንና ሕዝብን የሚያዋርድና የሚጎዳ አሳፋሪ ታሪክ ጥሎ ማለፍ በመጭው ትውልድና ታሪክ ዘንድ እየተኮነኑ መኖር እንደሆነ ላስመዘግብ እወዳለሁ።

<u>መለሰና ተባባሪዎቹ፡-</u>

1. ኢትዮጵያ በጎሳ እንድትከፋፈል የራሳቸውን ዕቅድ አውጥተው በተግባር እየተረጎሙ ናቸው።
2. ዜጎቿንም በዘር፥ በቋንቋና በሃይማኖት በመከፋፈል እርስ በእርስ እንዲተላለቁ ጥረዋል። ይህ ዕኩይ ተግባራቸው ግን አልሰራላቸውም። ይህም ሊሆን የቻለው፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅነትና አርቆ አስተዋይነት ብቻ ነው።

3. የሀገራችን የውጭ ዲፕሎማሲ ከመቸውም በበለጠ እንዲዋረድ አድርገዋል። የኢትዮጵያን ልዕዋላዊነትም የባዕዳን ተገዥ እንዲሆን አድርገውታል። ሀገራችን ዛሬ ከማንኛው ወቀት በበለጠ የባዕዳን መፈንጫ ሆናለች።

4. የዕልፍ አዕላፍ ዜጋ ደም በከንቱ አፍስሰዋል። የተቃዋመሚ ፖሊቲካ መሪዎችን፥ ነፃ ጋዜጠኞችንና የኅሊና እስረኞችን በማጎሪያ ውስጥ አስገብተው አሰቃይተዋል። በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ከሀገር እንዲሰደድ አድረገዋል። በብዙ ሽ የሚቆጠሩ ሕፃናት ሴቶች ልጆቻችንን ወደየዐረብ ሀገሮች ለውርደት እንዲሸጡ አድርገዋል። በዚህም የኢትዮጵያን ሕዝብ አሳፍረዋል። ሀገራችንንም አዋርደዋል።

5. በወያኔ መሪዎች በነመለስ ዜናዊ አምባገነን ሥርዓት ሥር የምትማቀቀውን ሀገር ነፃ ማውጣት የሚቻለው፥ ማነኛውን ዜጋ ለነመለስ ዜናዊ የሚሰጠውን ሁለንተናዊ ድጋፍ በመሰረዝ፥ የሕዝብ ወገንተኝነቱን ሲገልጽ ብቻ ነው።

ይህ በመሆኑ ወያኔን የምትደገፉ የትግራይና የሌሎችም ክፍለ ሀገራት ተዎላጆች ከዚህ ሀገር አጥፊ ብድን ጋር ያላችሁን ዕትብት በጥሳችሁ ከባለ ታሪኩ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመቆም ሀገራችሁን ከጥፋት በማዳን አኩሪ ተግባር እንድትፈጽሙ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በአንድነቷ በነፃነት ለዘለዓለም ትኑር።